

32-2

# ከአሉባልታ ወሬ እንሸሽ

## 4) እራስን ከፍ ለማድረግ

በትክክለኛው መንገድ መቅደም የሚያቅተው ሰው ሌላውን በመጥለፍ ቀድሞ ለመሄድ ይሞክራል። “ያንግ” የተባለው ሰው “ሰው በውስጡ ምን ያህል ትልቅ የተፈጥሮ ችሎታ እንዳለው ቢያውቅ ኖሮ በዓለም ላይ ቅናንትና ምቀኝነት አይኖርም” አለ። እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን የተለያየ የተፈጥሮ ችሎታ በውስጣችን አስቀምጧል። አንዱ ከሌላው በአንዳንድ ነገር የሚሻልበት በአንዳንድ ነገር ደግሞ ወደ ኋላ የሚቀርበት አለ። በአንዳንድ ሁኔታ ላይ ከእርሱ የተሻለ ሰው ሲያይ በዚያ ሰው ችሎታ በመጠቀም ፈንታ ሊያጠፋው ቢሞክር ብልህነት አይደለም። እራሱን ከፍ የማድረግ ችግር ያለበት ሰው ሌላውን ማመስገን ያቅተዋል። እራሱ ማመስገን አለመቻሉ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ሲያመሰግኑት መስማት ያስቆጣዋል። ለምሳሌ “እግዚአብሔር ይመስገን እከሌ እኮ ጥሩ ሰባኪ ነው። ሲሰብክ የልብ ነው የሚያደርሰው” ሲል አንዱ አስተያየት ይሰጣል። እራሱ ብቻ እንዲመሰገን የሚወድ ሌላው ደግሞ የዚያን የተመሰገነውን ሰው ስምና ዝና በሴንጢ መቆራረጥ ይጀምራል። “አይ የኔ ወንድም! ፑልፒት ላይ ብቻ መጮኹ ብቻ ምን ያደርጋል? ከፑልፒት ሲወርዱ ሌላ ዓይነት ሕይወት እየኖሩ ምን ይጠቅማል?” በማለት በሌላው ሰው ልብ ውስጥ ስለዚያ ሰባኪ ጥርጣሬን መዝራት ይጀምራል። ያም ሰው “ምነው ስለ እርሱ አንተ የምታውቀው ነገር አለ እንዴ?” ሲል ይጠይቃል። ሲመልስለትም የተነሳው በተንኮል ስለሆነ “አይ! እባክህን ተወው! ነገሩ ብዙ ነው! የሰው ኃጢአት ቢያወሩት ምን ይጠቅማል? የሰውን ኃጢአት ብናወራው ለማንም ጸጋ አይሰጥምና እንዲያው እንተወው” ይላል። አድማጩም “እንዲያው ብዙ ነው” ሲል አስተያየት የሰጠውን ሰው “ያ ብዙ ነው ያልከው ነገር ምንድነው?” ብሎ ተጭኖ አይጠይቅም። “ብዙ ነው” ያለውን ብቻ ተቀብሎ ይሄድና እርሱም በተራው ለሌላው ሰው “የእከሌ ኃጢአት እጅግ ብዙ ነው” ሲል ያወራል። ምናልባት የሚቀጥለው ሰሚ “እጅግ ብዙ ነው ብለህ በደፈና አትንገረኝ፤ አንዱን ብቻ እንኳን ንገረኝ” በማለት ወጥሮ የሚይዝ ከሆነ ያ ሰው ጉድ ይፈላበትና የሚመልሰው መልስ ሲያጣ “ያባቱን ሚስት አገባ” ሲል የፈጠራ ወሬ ያወራል። በዚህ መልክ የአሉባልታ ወሬ ይስፋፋል።

የአሉባልታ ወሬ መስፋፋት ብቻ ሳይሆን፥ ያለአግባብ በምቀኝነትና በቅናት ተነሳስተው አንዳንድ ተንኮለኞች በሚረጩት ወሬ በክርስቲያኖች መካከል እውነተኛ ፍቅርና አንድነት መጥፋቱ ያሳዝናል። እንዲሁም ግሩምና ድንቅ የሆነ ልዩ ልዩ ችሎታ ያላቸው ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ስጦታቸውን ለቤተክርስቲያን እድገት እንዳያውሉት ወደ ጎን ተገፍተው ይቀራሉ። በዚህም የሚጎዱት እነዚያ የተገፉት ሰዎች ብቻ ሳይሆን ቤተክርስቲያንም ጭምር ነች። ሌሎችን በማሳነስ የራሳቸውን ትልቅነት ለማሳደግ የሚሞክሩ ሰዎች አሉ። ሌላውን ዝቅ አድርገውና አሳንሰው የሚያወሩ ሰዎች እራሳቸውን ከሰማይ እንደ ወረዱ አድርገው ለማቅረብ የሚሞክሩ ሰዎች ናቸው።

### 5) ሌላውን ለመጉዳት

አሉባልታ፥ የሚጠሉትን ሰው በግልጽ ለመጉዳት ድፍረት የሌላቸው ሰዎች በድብቅ የስም ማጥፋት ዘመቻ በማውራት የሚጎዱበት መሣሪያ ነው። የአሉባልታን መጥፎነት የሚናገር አንድ ሰው እንዲህ አለ። “ባልሰለጠኑት አገሮች ውስጥ በተለይም በዋሻ ውስጥ የሚኖሩ አንድንድ ብሄረሰቦች ሰው እያረዱ የሰው ሥጋ መብላታቸውን ትተዋል። በሰለጠኑት ሕዝቦች መካከል ግን ሰው እያረዱ የሰው ሥጋ የመብላት ልምምድ ግን በየጊዜው እያደገ ነው። ሰው አርዳችሁ ዛሬ የሰው ሥጋ ጥሩ አድርጌ ጠብሼ አዘጋጅቼአለሁና፥ ኑና ተጋበዙልኝ ብላችሁ ጎረቤቶቻችሁን ብት ጠሩ ሁኔታው ዘግንኗቸው ግብዣችሁን የሚቀበል ሰው አታገኙም ነበር። በዚያ ምትክ ግን፥ የአንድነት ጊዜ አዘግጅቻለሁ ብላችሁ የአንዱን እዚያ ያልተገኘውን ሰው ስም ክብርና ዝና እንደ ሥጋ አቅርባችሁ አጥንቱን እንዲግጡ ብታቀርቡላቸው እንግዶቻችሁ ጣፍጧቸው ግሩም ድንቅ ግብዣ ነው ብለው ይወጡ ነበር” ሲል ተናገረ።

አሉባልታ ይበልጥ ጎጂ የሚሆነው አሉባልታውን የሚጠቀምበት ሰው ሽፋፍኖና አሰማ ምሮ ስለሚያቀርበው ነው። ሲናገር ስለ ቤተክርስቲያን ተቆርቋሪ ይመስላል። “በእግዚአብሔር ቤት ኃጢአት እንዳይሰለጥን እንድንጠበቅ ኃላፊነት አለብን” በማለት የቤተ ክርስቲያን የሕይወት ጽዳት ተቆጣጥሪ እንደሆነ አድርጎ እርሱን ያቀርባል። ወይንም እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን “በመጥረጊያ እየደበደብክ አስወጣ” ብሎ ልዩ ስልጣን ከላይ እንደተሰጠው አድርጎ እራሱን ያቀር ባል። “የቤትህ ቅናት በላችኝ” የሚለውን ጥቅስ ከመጽሐፍ ቅዱስ አለአግባብ ቦጭቆ በማውጣት ሊጠቀምበት ይሞክራሉ። እንደ እውነቱ የበላው “የራሱ ቅናት” ብቻ ነው።

<u>አሉባልታ ኃጢአት ነው</u>

ክርስቶስ በተራራው ስብከቱ “በእናንተ ላይ እንዳይፈረድባችሁ በማንም ሰው ላይ አትፍረዱ ምክንያቱም በሌሎች ላይ በምትፈርዱበት ዓይነት በእናንተም ላይ ይፈረድባችኋል እንዲሁም በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ይሰፈርባችኋል” አለ (ማቴ. 7፥1-2)። ሁላችንም በሌሎች ስህተት ላይ የማትኮር ሌሎችን የመንቀፍና በሌሎች ላይ የመፍረድ ዝናብሌ አለን። ይሁን እንጂ ኢየሱስ ማናችንም በማንም የመፍረድ ኃይልና ስልጣን እንደሌለን ይናገራል። ይህን ብናደርግ እኛም ከስህተት የራቅን ስላልሆንን የራሳችንን ውድቀት በማስተካከል ፈንታ የሌሎችን ሕይወት ለማጥራት ስንሞክር “ግብዞች” ያሰኝናል። ሃዋርያው ያዕቆብ ከአሉባልታ መራቅ እንደሚገባን ያስተምረናል። “ወንድሞቼ ሆይ! እርስ በርሳችሁ አትተማሙ፤ ሰውን የሚያማ ወይም በሰው ላይ የሚፈርድ ሕግን ያማል፤ በሕግም ላይ ይፈርዳል፤ በሕግም ላይ ብትፈርድ ፈራጅ መሆንህ ነው እንጂ ሕግን ፈጻሚ አይደለህም” ይላል ያዕቆብ 4፥11 ላይ። ስለዚህ መፅሀሕ ቅዱስ በግልጽ “አታድርጉ፤ አትፈጽሙ፤” የሚለንን ትዕዛዝ ችላ በማለት በአሉባልታ ሕይወት ብንመላለስ ኃጢአት መሥራታችን መሆኑን እንዳንዘነጋ ያስፈልገናል። ኢየሱስ “በማንም ላይ አትፍረዱ” ሲለን በቤተክርስቲያን ውስጥ መቀጣት መገሰጽ የሚገባው “ሳይገሰጽ ይታለፍ” ማለቱ አይደለም። መታረም የሚገባው ሰው ቢኖር እንዴት መታረም እንዳለበት ቅደም ተከተሉን በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 18 ላይ በሚገባ ተጠቅሷል። አልፎ አልፎ ስለ አንዳንድ ሰዎች የግድ መነገር የሚገባው ጊዜና ሁኔታ ይኖራል። አሉባልታ ወይንም ተራ ሀሜት መሆን አለመሆኑ የሚለካበትና የሚመ ዘንበት መንግድ አለ። ይኸውም፥

*ሀ) መስማት ያለበት ሰው ማን ነው?*

ወሬው ወይንም መግለጫው የሚነገረው ሰው ማን ነው? ነገሩ እርሱን ይመለከተዋል? የዚያን ሰው ታሪክ እንዲያውቅ የተፈለገበት አጥጋቢ ምክንያት አለ? በሽምግልና ከማገለግልበት ቤተክርስቲያን በቅርቡ የቤተክርስቲያኒቱ መጋቢ ስብሰባ ጠርቶን ከምዕመናችን መካከል አንዱ በከፍተኛ ኃጢአት መውደቁን ገለጸልን። እንድናውቀው የተደረገው የቤተክርስቲያኒቱ መሪዎች በመሆናችን ለዚያ ሰው እንድንጸልና እንዲሁም ልንወስደው የሚገባንን እርምጃ ለመወያየት ነበር። ይህ መጥፎ ዜና አግባብ ባልሆነ መንገድ እንዳይራባ እኛ የቤተክርስቲያኒቱ ሽማግሌዎች ሌላው ቀርቶ ለሚስቶቻችንም እንኳን ታሪኩን አልገለጽንም። በዚህ አጋጣሚ ላሳስብ የምፈልገው የቤተክርስቲያን አባሎቻችን እንድንጸልይላቸውና እድንመክራቸው ችግራቸውን ሲያዋዩን ሚስ ጥራቸውን እንደምንጠብቅላቸው አምነውን ነው። እኛም የጣሉብንን አደራ ሳንረሳ ምስጢራ ቸውን መጠበቅ ያስፈልገናል። የቤተክርስቲያን መሪዎች ሆነን ምስጢር መያዝ ባለመቻላችን የተነሳ ብዙ ጊዜ ብዙዎቻችን የአሉባልታና የሀሜት ምክንያቶች እንዳንሆን መጠንቀቅ ይገባናል። አባሎቻችን ምስጢራቸውን የማንጠብቅላቸው ከሆንን ሁለተኛ ችግራቸውን ለእኛ መጥተው ማካፈል ድፍረት ስለማይኖራቸው ከክርስቲያኖች ሸሽተውና ገለል ብለው ይኖራሉ።

*<u>ተናጋሪው በምን ስሜት ነው የሚያወራው?</u>*

ታሪኩን የሚናገረው ሰው በምን ዓይነት ሁኔታ ሆኖ ነው? ነገሩ ልቡን ሰብሮት እያዘነ ነው? እየጨነቀው ነው የሚናገረው? ወይንስ የዚያን ሰው በደል ደስ ብሎት ነው የሚያወራው? ጉዳዩን ከሌላው ሰው ጋር ከመነጋገሩ በፊት ከራሱ ከሰውየው ጋር ተነጋግሮበታል? እያዘነና እየተጨነቀ ከሆነ የሚያወራው ወሬው አሉባልታ ወይንም ሀሜት አይሆንም።

*<u>የሚያወራበት ምክንያት ምንድነው?</u>*

ወሬው የግድ አስፈላጊ ካልሆነ ወይንም ዓላማ ከሌለው አሉባልታ ወይንም ሀሜት ይሆ ናል። ወሬውን እንዲሰማ የሚፈለገው ሰው ምን እንዲያደርግ ነው? ብዙ ጊዜ አሉባልታ የሚያስ ፋፋው "ለእከሌ እንጸልይለት" በሚል ዘዴና ጥበብ ነው። ይሄ አባባላችን እውነትነቱን የሚመዝ ነውና የሚፈርደው እግዚአብሔር ብቻ ነው። እግዚአብሔር የምንናገረውን አይቶ በንግግራችን እርሱ ይፈርድብናል። "በእውነት እላችኋለሁ፥ ሰዎች በሚናገሩት ምንም ጥቅም በሌለው ከንቱ ቃል ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል። ምክንያቱም ከቃልህ የተነሣ ይፈረድልሃል፤ ከቃል ህም የትነሣ ይፈረድብሃል" ይላል (ማቴ. 12፥36-37)።

*<u>አሉባልታ (ሀሜትን) እንዴት እናስቆም?</u>*

የብዙዎች ችግር አንድ ሰው ስለ ሌላው ሰው ሲያወራ የሚሰጡት መልስ ማጣት ነው። "እባክህን ስለ ሰው አታውራ" ብሎ መናገር ያንን ሰው ማስቀየም ይሆናል። መልስ ሳይሰጡ ዝም ማለት ደግሞ አሁንም ሰውየውን ማሳፈር ይሆናል? ታዲያ ምን መመሪያ ይኖር ይሆን? ከዚህ ቀጥሎ አንዳንድ ሀሳብ ለመስጠት ሞክረናል።

1) "እርስ በርሳችሁ አትተማሙ" የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል እንዳንጥስ አስቀድመን እን ጸልይ። ዳዊትም "እግዚአብሔር ሆይ! ለአፌ ጠባቂ አኑር፤ በከንፈሮቼም በር ላይ ዘበኛ አቁም" ሲል ጸልዮአል።

2) ስለ ሌላ ሰው ሲወራልን በተቻለ መጠን በዘዴና በጥበብ የንግግሩን አርዕስት ለመቀይር እንሞክር።

3) የምንሰማውን ወሬ "አሜን" ብለን ከመቀበል ይልቅ በዚያ ሰው ወገን ሆነን እንከራከርለት። ለምሳሌ፥
አውሪ፥ "ድፋባቸው መንፈስ ቅዱስን ክዱል አሉ"
ሰሚ፥ "በምን አወቅህ? ማን ነገረህ?
አውሪ፥ "ብዙዎች ያወራሉ"
ሰሚ፥ "አንተ እራስህ ድፋባቸውን አነጋግረኸዋል? ጠይቀኸዋል? አውሪዎቹ በምን ዓላማ ተነሳ ስተው እንደሚያወሩ ተረድተሃል?"
አውሪ "አላውቅም" ይላል። በዚህ ሁኔታ ያ ሰው መልስ መመለስ ያቅተውና የንግግሩን አርዕ ስት ይለውጣል። ለሁለተኛ ጊዜም አሉባልታ ይዞ አይመጣም።

4) እቤታችን ሰዎች ጋብዘን እንደሆነ ተሰብስበትን በመካከላችን ስለ ሌላ ሰው እንዳናወራ አስቀድ መን እንግዶቻችን ከመጣታቸው በፊት ፕላን እናውጣ። የጸሎት ጊዜ ጌታ በሕይወታችን ያደ ርገውን ነገር የምንነጋገርበት ጊዜ፥ ጊዜ ከበቃን ደግሞ ልዩ ልዩ ጨዋት (ጌም) የምንጫወ ትበትን ፕሮግራም ማቀድ እንችላለን። በዚህ መካከል ስለ ሌላ ሰው አሉባልታ የምናወራበት ጊዜ አይኖረንም። አሉባልታ ቢጀመር እንኳን ጋባዦቹ እኛ ስለ ሆንን የውይይቱን አቅጣጫ መቀየር እንችላለን።

5) ክርስቲያኖች ብዙ ጊዜ አሉባልታ (ሀሜት) የምናወራበት ጊዜ የጸሎት ፕሮግራም ሲኖረን ነው። "የጸሎት ፕሮግራም" ከምንለው "የአሉባልታ ወይንም የሀሜት ማውሪያ ጊዜ" ለምን አንለ ውም? "ለእከሌ እንጸልይለት" በሚል ሀሳብ የዚያን ሰው ችግር ማውራት እንጀምራለን። ሰውየው እራሱ ፈቅዶ "እንዲጸልይልኝ ንገሩልኝ" ካላለ "ለእከሌ እንጸልይለት" በማለት የሰው የውን ታሪክ መዘርዝር የሀሜት ወይንም የአሉባልታ ማስፋፊያ ምክንያት መሆናችንን አንርሳ።

6) ብዙ ጊዜ ሀሜት ውስጥ የምንገባው የምናወራበት አርዕስት ስናጣ ነው። ለዚህ መድኃኒቱ በዕ ለቱ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተማርነውን ባለፈው ሳንም ሰባኪው ሲሰብክ ያገኘነውን አዲስ ሃሳብ ካነበብነው መጽሐፍ ያገኘውን ትምህርት የልጅነት ታሪካችንን (የሚያስቀውንና የሚያሳዝ ነውን) ታሪክ መወያየት እንችላለን።

7) አሉባልታ ወይንም ሀሜት ማውራት ልማዳችን ከሆነ ምንም እንኳን የሚሰማን ሰው ደፍሮ ባይናገረንም፥ በልቡ ግን እንደሚታዘበን እንወቅ። ያ ሰው እኛን የሚያየን የፍቅር ሰዎች አለ መሆናችንና የሰው ስህተት ለቃሚዎች መሆናችንን ነው። በምናወራው ወሬ ሰዎች ይታዘቡ ናልና ጠንቀቅ እንበል።

……………………………………………………………………

**በሚቀጥለው ክፍል እንክንገናኝ፥ የጌታ ጸጋና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን።**